# ጉድ ሳይሰማ ፣ መስከረም አይጠባ!

August5,2010 በዋሽግተን አሜሪካ በኋት ሐውስና በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የተደረገውን ስልፍ ተመልክቻለሁ። አዘጋጆቹ ከቀረቡላቸው ቃል መጠይቆች እንደተረዳሁት፡ በሥልጣን ላይ ያለው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ መንግሥት ደጋፊዎች መሆናቸውን ነበር።

ለአሜሪካ መንግሥት ያቀረቧቸው መጠይቆች የሚከተሉት ነበሩ።

1ኛ አሜሪካ ግብፅ የአባይ ወንዝን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ላይ የምታደርገው ተጽኖ ታስቁም።

2ኛ አሸባሪዎች በዩጋንዳ ያደረጉት የሰው ሕይወት ጥፋት እናወግዛለን፤

3ኛ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ወያኔን ጭላት መቀባቱን ያቁም።

4ኛ በግንቦት 2002 ዓመተ ምህረት የተካሄደው ምርጫ ፍህታዊና ሰላማዊ ነው።

ይህ ነበር፣ለአሜሪካ ፕሬዘዳንት አቦማና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ለሒነሪ ኪልተን የቀረበው አቤቱታ።

ለያንዳንዱ መጥይቅ ትንታኔዬን ከማቅረቤ በፊት በሕብረተሰባችን ውስጥ ቅርጹን እየቀያየረ ሰለሚመጣው አንድ መጥፎ ባሕል  ትንሽ ልበል።

ተውልጄ ባደኩበት አካባቢ ነው። ከአካባቢው ክፍ ብሎ የሚታይ ኮረብታ አለ።  በዚያ ኮረብታ ላይ አካባቢውን የሚያስተዳድሩት ሹመኞች የሚኖሩበት ቤት ተሰርቶላቸዋል። ቤተ መንግሥት ይባላል። አስተዳዳሪዎቹ ደስ ባላቸው ጊዜ ዳስ ጥላው ያካባቢውን ሕዝብ ግብር ያበላሉ። እነኝህ አስተዳደሪዎች ከሕዝቡ ምንም ግንኙነት የላቸውም። በዓመት ውስጥ ሁለቴ ወይም ሦስቴ የራሳቸውን ክብር ለመግልጽ በየደረጃው ጠርተው ግብር ያበላሉ።ከሕዝብ ውስጥ ብልህ አይታጣምና ይህ ሁኔታ ክብራቸውን የነካው ግለሰቦች ጥያቄ ያነሳሉ። ጥያቀውም እንዲህ ነበር። ‘የአስተዳዳሪያችን ፊት የምናየው ግብር ለመብላት ስንጠራ ብቻ ነው። አስተዳደሪያችን  በሳቸው ደረጃ እንደሰው ሳያዩን  እርስቸው ግብር አግቢ እኛ ግብር በይ ነን ይህ ክብር አይነካም? ጅብ ሲመጣ እንዲጮህ ለውሻ ቅንጥብጣቢ ይጣልለታል ፤ ጌታውን ከታሰበበት እንዲያደርስ  ለፈረስ ወይም ለበቅሎ ጥሬ ይቀርብለታል። እኛ ሰዎች ነን ግብር ስለገባልን እንደውሻ እንደፈረስ እንደበቅሎ የግለሰብ አገልጋይ ሎሌ አንሆንም’ በማለት ሕዝብ ያሳድማሉ።

እንደተለመደው ሹመኛው ፋሲካን አመካኝታው ድል ያለ ድግስ አሰደገሱ። ፊርዳው ቀረበ፣ ጠጁ ተጣለ፣ ጠላው ተጠመቀ፣ እንጀራው ተጋገረ፣ በመቶዎች የሚቆጠር ሰታቴ ተጣደ፣ ወጡ በባለሞያዎች ተሠራ። ዱካኑ በስፋት በብዛት ተጣለ። ካሽከር ከገረዱ ጋር የሕብረተሰቡ ኗሪ በዝግጅቱ ተሳተፈ። ዕለቱና ሰዓቱ ሲቃረብ አካባቢው እረጭ አለ።ሕዝብ ቢጠበቅ ቢጠበቅ አይመጣም። ያለውም የሌለውም እንደአቅሙ በሽሮው ላይ ቅቤው ጣል አድርጎ ጾሙን ገደፈ። ሆድ አደር አለመሆኑን አሰመሰከረ፣ እንደሹመኛው እርሱም እኩል ሰው መሆኑን አሣየ።

አስተዳዳሪውም አንተ ሕዝብ ወርጅ ይግዛህ ብለው ተራግመው ሥጋውን ለአሞራና ጅብ፣ ጠጅና ጠላው ከኮረብታ ቁልቁል ሲደፉ አካባቢውን እንደወራጅ ውኃ አጥለቀለቀው።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ተክለማርያምን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሎሌዬ ነህ ሲሏቸው ፍርጥም ብለው አይደለሁም ያሉ የሰው ልካቸውን ያወቁ ሰው ነበሩ። ይህም ‘የሕይወቴ ታሪክ’ በሚለው መጽሐፋቸው 1998 ዓ ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታተመው ውስጥ ተጠቅሷል።

ግብር ማግባቱ ፋይዳው ከግብርበላው ውስጥ ሎሌ ለመመልመል ስለሆነ፣መለስ ዜናዊም በዚህ ዓመት ሁለት ጊዜ ግብር አብልቷል። ግብርበላዎችም ተገኝተዋል። አንዱ የምርጫው ኮድ ከተፈረመ በኋላ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከምርጫ 2002 በኋላ ለፓርላማ አባላት ለነበሩ ያገባው ግብር ነበር። ግብርበላዎቹም ሰው ከቁጥር ጎደለብን ሳይሉና ሳያቅማሙ፣ለግብርበላነት ቀርበዋል።

ይህ ግብር ማግባትና ለክፉ ቀን ከግብር በላው ውስጥ ሎሌ መመልመል ሲሆን መስፈርቱም ለራሱ ክብር የሌለው ሆደም መሆን ነው። ያመላመሉ ዘዴ ይለያይ እንጂ  በንጉሱም በወታደር መንግሥቱም  ነበር።በየንጉሡ ነገሥቱ ዘመን ከማንኛው አካባቢ ሎሌ መልመል ይቻል ነበር። በወታደራዊ መንግሥት ወደወታደሩ ያዘነበለ ነበር። በወያኔ መንግሥት ደግም የሎሌው ምልመላ ያተኮረው በአንድ ጎሳ ላይ ነው።   በዋሽግተን ኦገስት 5፡ 2010 ዓ ም የተደረገው ሰልፍም ያንን ፍትው አድርጎ የሚያሳይ ነበር። ይህ ያረጀ ያፈጀ ባሕል ያለቀቃቸውን የወያኔ መሪዎችና ተከታዮች ግብር በላዎችን  ከኋትሐውስ በር ላይ እንዲሰለፉ  አድርጎ ገበናን  ለዓለም ሕዝቦች አሳይቶ በሃገራችን ሕዝብ ላይ እንዲሳለቁባት ማድረግ ከሆነ የሃገራችን ጉዳይ የሚከነክነን አንድነት እስከምንቆም ድረስ ይሁን ከማለት ሌላ ምን ይደረጋል።

መግቢያ ላይም መልኩን እየቀያየረ ይመጣል ያልኩት መጥፎ ባሕል ይህ ሲሆን ከሰውነት ወደ ውሻና በቅሎ ዝቅ የሚያደርግ ነው።

ለዚህ ሁሉ የቅሌት የውርደት መንስኤውን ገልጫለሁ። መንስኤው ለመነሻው ለመድረሻውም ያው ሰው ነው። ለአሜሪካ መንግሥት የቀረቡት መጠይቆች ያለቦታቸው ሲሆኑ ከዚህ በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ መሥፈርታቸውን ያሟሉ የሕዝብን ብሶት የሚያጸባርቁ ሰልፎች በኢትጵያውያን የተደረጉትን ወደፊት የሚደረጉትን ልማዳቸው ነው ተብሎ ክብደት እንዳይጠሰቻው ለማድረግ ነው።

የዐባይን ወንዝ አስመልክቶ የአሜሪካ መንግሥት የሚያገባው ያለ አይመስለኝ። የወያኔ መንግሥትም ቢሆን ከአሜሪካ እኩል ከሊግ ኦፍ ኔሽ 1919 ዓ ም ጀምሮ የተባበሩት መንግሥታት መስራች የሆነችው ኢትዮጵያ በሃገራት መካከል ችግር ቢፈጠር የምትሄድበትን አታውቅም ማለት አይቻልም። ለኔ ገን ሰልፉ የልጅነቴን የምድጃ ሥር ጫወታ አስተወሰኝ። 'ኩኩ መለኮቴን'
ኩ ኩ መለኮቴ እሷ በፈሣችው በኔ ላከከችው፣

አባ ተቆጡልኝ እማ ቆንጥጡልኝ። አባም ፕሬዘዳንት ኦቦማ መሆናቸው ነው፣ እማም ሚስ ኪልንተን።

## ወይ ጉድ! ጉድ ሣይሰማ መስከረም አይጠባ!

ለዩጋንዳው የአሻባሪዎች ጥቃት መንስኤውን እንኳንስ የአሜሪካ መንግሥት ተሰላፊዎቹ ሎሌዎቹ እንክት አድርገው ያውቁታል። የሃገሬ ኦሮሞ ሰለሚያውቀው ነገር ደጋግው ሲነግሩት፣'ኡዱ ዲሲ ወጢ ባሲ' ይላል። ወሬውን ትይና በጅሺ ያለውን ወጡን አውጪ ማለት ነው።

ስብአዊ መብት ተካራካሪዎችን ማውገዙ ለምን የጋቢላው እልቂት ተጋለጠ፡ በምርጫ ስም ሰልፍ የወጡትን ሕፃን ወጣት አረጋውያን በአጋዚ ጦር ተገደሉ፣ የኦጋዴን ሕዝብ በጅምላ ተጨፈጨፈ፣ በባድሜ ጦርነት ላይ የተሰውት ወገኖች አፈር የሚያለበሳቸው ጠፍቶ የአሞራ ምሣ የጅብ እራት መሆናቸውን በማጋለጡ ይመሰገናል እንጂ ይወገዛል። አምናለሁ የአንድ ሃገር ሕዝቦች ነንና ከተሰላፊዎቹ ውስጥ የሚቾ ዘመዶች አይታጡም። ሰው ለሆዱ ካደረና ሎሌ ከሆነ አእምሮው ቀጭጮ እንደፈረስ እንደበቅሎ በሰው ይመራል።

የምርጫውን ፍህታዊነትና ሰላማዊነት ምን ሌላ መግለጫ አስፈለገው፣ ለዘመኑ ተክኖሎጂ ምስጋና ይግባውና፣ የወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ጥይት በማይበሳው መስታወት ተከልሎ ለአዲስ አበባ ኗሪዎች በመስቀል አደባባይ ያሳየው ትዕይንት ልጅ ሆነን የምንጫወተውን 'ያቆብ የት ነው ያለህው የሚለውን አስታወሰኝ። ዙሪያው ልጆች ከበው ሁለት ልጆች እንዳያዩ ዐይኖቻቸው በጨርቅ ተሸፍኖ ቀበቶ ወይም አለንጋ ይቀመጣል። አለጋውን ቀድሞ ያገኘ 'ያቆብ' እያለ ይጣራል። ያም በማጨብጨብ ያለበትን ያመለክትና ወዲያውኑ በመሸወድ አቅጣጫውን ይለወጣል። ዘሎ እንዳይወጣ ክብ ሠርተው የተቀመጡት አጥር ነው አጥር ነው እያሉ አለንጋ የያዘው እንዲደበድበው ውደ ውስጥ ይመልሱታል።

ኦገስት 5 2010 በዋሽግተን የተደረገው ሠልፍ የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ካሣዩን ትዕይንት ያነሰ መሆኑ የተመልካች ቁጥሩ ፍንትው አድርጉ አሣይቷል።

ያም ሆነ ይህ ቀልዱን ወደ ጉን ትተን በሰከ አእምሮ ከደጋፊም ክፍል ሆነ ከተቃዋሚ ነገ ልጆች ለምንወልድ ለወለድን አባትም እናትም ለሆንን ተኪዎቻችን የልጅ ልጆቻችን እንዲኖሩባት የምንፈቅደው ይህቺ ዛሬ የምናያት ኢትዮጵያን ናት? ይህ የያንደንዳችን ራዕይ ነው? ጥያቀውንም መልሱንም ለራሳችን እንየው። ይህ ለሎሌነት ማደር ከዛሬ ሰባ ስልሳ ዓመት በፊት ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለመርያም የቱን ያህል እንዳሳሰባቸው እኛ የዛሬዎቹ ይህ ችግር እንደሚገጥመን አውቀውት ነበር። ለመለወጥ ያደረጉትም መፍጨርጨር በሕይወታቸው ላይ ብዙ መስቅልቅል ፈጥሮባቸዋል። ኢትዮጵያ በሰባ ዓመት ውስጥ ብዙ የተማሩ ሌሂቃን አፍርታለች። ምሁራኖች ዛሬም ወፎ ቆሞች በመባል ላይ ናቸው ወይስ ገና በዳዴ ላይ! ዛሬ በሃገራችን ቻይናዎች አረቦች ሕንዶች ፓክስቲያኑ ወዘተ ብር ይዘው የመጡ ነገ ንብረታቸውን የሚጠብቅ ወታደር ላለማምጣታቸው ምን ዋስታ አለን? አሁንም ወደ ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ልመልሳችሁና በጊዜው የነበሩት የንጉሡ ግብርበላዎች ለንጉሡ ምቾት መጠበቂያ ከውጭ ገንዘብ ካልተበደርን ብለው ያስቸግራሉ።' ዛሬ ብር ያበደሩን ብሩ በምን ላይ እንደዋለ ለማየት ብለው ወታደር ቀስበቀስ ላለማስገባታቸው ምን ዋስተና አለን?' ይህ ነበር ጥያቄአቸው። የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከቻይና እስር ቤት በቀጥታ ስለወረሯትና የሃገሪቱ ዜጎች ከወሻ ካልተናነስ ኑሮ ሲኖሩ የቀሩትም ሃገራቸው ከሚቀራመቱት አረብ አገሮች በባርነት መሸጣቸው ምንድነው የሚያሳየው?

ይህን ማቃለል የምንቸለው በራሳችን የምንተማመን ሌላው ከእኛ ጋር እኛም ከሌላው ጋር በሰው መሆናችን ተማመን ሥንሰራ ብቻ ነው።

## ታደለ መከሪያ